# የተቃዋሚ ሃይሎች በወያኔ ቧልት እንዳይዘናጉ ጥሪ ቀረበ

በሳን ሆዜ ካሊፎርኒያ በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ የድጋፍ ኮሚቴ እና የአካባቢዉ የኢሕአፓ አካል ትብብር በግንቦት 18, 2010 የተጠራው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ በእንግድነት የተገኙት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከፍተኛ አመራር አባል የሆኑት አቶ ፋሲካ በለጠ በአዲሱ የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስቴር አማላይ ዲስኩር ተቃዋሚ ሃይሉ መዘናጋት እንደሌለበት እና ትግሉን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጥሪ አቅርበዋል።

ላለፉት በርካታ አመታት በህዝባዊ እንቅስቃሴ እና ትግል በከፍተኛ ደረጃ ተወጥሮ የነበረው ወያኔ የተወሰኑ እስረኞችን በመፍታት እና መሠል ጥገናዊ ለዉጦች በማድረግ ትግሉን አቀዝቅዞ ህዝብ የተንገሸገሸበትን ስርዓት ለማስቀጠል ከፍተኛ ሙከራ እያደረገ ነው ያሉት አቶ ፋሲካ በለጠ ስርነቀል ለውጥ ተደርጎ የሺግግር መንግስት እስከሚመሠረት ድረስ ትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አስገንዝበዋል።

በስብሰባው የተሳተፉ ወገኖች በርካታ ጥያቄወች አቅርበው ተገቢ እና አጥጋቢ መልሶች ተሠጥቷቸዋል። ስብሰባውም በጥሩ መንፈስ እና መግባባት ተጠናቆል።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!
ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘላለም ትኑር !!

Bay Area Finote Support Committee

bayareafinote@gmail. Com

May 28, 2018

• • •